አቤቱ ምድርህን አስብህ፡ ሃሌ ሉያ፡ ጸሎታችንንና ልመናችንን ስማ። ኃጢአታችንንም ሁሉ አስተስርይልን። ጸሎታችንንና ልመናችንን ስማ። የእዝራን ጸሎትና ልመና እንደሰማኸው፡ ምሕላችንን ተቀበል። ሰላምህን ስጠን ከመካከላችን አትራቅ።
መዓትሕን ከእኛ መልስልን። ሃሌ ሉያ። ንግግርዋ ሁሉ ሰላማዊ የሆነ፡ ቃልዋ የሚጣፍጥ እናታችን ሆይ፡ ወደ እኛ ነይ።
ይቅርታህን አሳየን፡ ሃሌ ሉያ፡ የሰላማችን መልአክ የመላእክት አለቃ ሚካኤል፡ ስለእኛ ለምን፡ አማልድ፡ በገናናው ንጉሥ ፊት ጸሎታችን አሳርግልን።
ገብርኤል ለማርያም የምስራች ነገራት፡ በያዕቆብ ወገን ላይ ለዘለዓለሙ የሚነግሥ ልጅ ትወልጃለሽ፡ ለሰላሙም ፍጻሜ የለውም አላት።

ጊዮርጊስ ወደ እግዚአብሔር ለምንልን፡ ጸልይልን። ሰውነቱን አረዱት፤ ቆራረጡት፤ እንደ አመድም በተኑት፤ ወደሰባ ነገሥታት ወሰዱት፡ አባት ጊዮርጊስ ምድርን ረግጦ ሙት አስነሣ በሰላም መንግሥተ ሰማያትም ገባ ክብርንም ተቀዳጀ።
ብፁዕ አባታችን ተክለሃይማኖት፡ ከጌታው ዘንድ ዋጋውን ለማግኘት ገዳማትን ዞረ፡ በደስታና በሰላም ደብረ ሊባኖስ ገባ ።

አባ በረከትህን እንድንቀበል በቅድስት ቤተክርቲያን የሰላም በረከት ባርከን፡ አባ በረከትህን እንድንቀበል ባርከን።
የሰላማችን ማደሪያ የከበረች ድንኳን የመላእክት እህት ፤የሰማዕታት እናት ናት፡ ኑ ሁላችንም ለእናታችን ለማርያም እንስገድ።
መስቀል ለዓለም ሁሉ ብርሃን ነው፡ የቤተክርስቲያንም መሠረት ነው፡፡ ሰላምን ሰጪ መድኀኔዓለም ሆይ ሰላምህን ስጠን።

የእግዚአብሔር አብ ሰላም ፤የእግዚአብሔር ወልድ ሰላም፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሰላም ከሁላችን ጋር ይሁን።(3)

## አድነን

አድነን ሕዝብህን ባርከን፡ ርስትህንም ስምህን ለምንጠራ ለአገልጋዮችህ ድል መንሳትንና ኃይልን ስጠን፡ የወገኖችህን ልጆች ጠብቀን፡ በመላእክት ታዳጊነት በየጊዜውና በየሰዓቱ በመስቀልህ ኃይል እርዳን፡ በመስቀልህ ተቤዝን።
ስለ ባለሟልህ አብርሃም፡ ስለ ወዳጅህ ስለ ይስሐቅ፡ ስለ መረጥከው እስራኤል ብለህ አቤቱ ቃል ኪዳንህን አስብ፡ ይቅርታህን ፈጥነህ ላክ።የሕዝብህን ኃጢአት ማር፡ የእጅህን ፍጥረቶች እኛን ይቅር በለን። አቤቱ አታፋን።
በእናትህ በማርያም አማላጅነት፡አጥማቂህ በዮሐንስና በቅዱሳንህም ሁሉ አማላጅነት፡ ሁል ጊዜ በመስቀልህ ታዳጊነት እርዳን አቤቱ በፊትህ አታሳፍረን።
እመቤታችን ሆይ ወደ እኛ ተመልከቺ፡ ለእኛ ልጆችሽ ለምኚልን፡ ከችግርና ከሐዘን ሁሉ አድኚን።
ቀን ከኛ ጋር፡ ሌትም በመካከላችን ሁን። አቤቱ አንተ ከእኛ አትለይ፡ ከእኛ ጋራ ኑር፡ ረዳትም ሁነን፡
አትተወን፡ አትናቀንም፡ የሰላም አምላክ ሆይ ተራዳን።
አትተወን፡ አትተወን፡ አትናቀንም፡ የሰላም አምላክ ሆይ ተራዳን።(2)
እመቤታችን፡ እመቤታችን ሆይ፡ ወደ እኛ ተመልከቺ፡ የልጅሽም ሰላም በእኛ ላይ አድሮ ይኑር። (3)